# ለስጋ ማሸግያ ፋብሪካ የተደረጉ የኮቪድ-19 (COVID-19) የጤና ጥበቃና ደህንነት መመርያዎች

*በኮቪድ -19 (COVID-19) ምክንያት በስራ ገበታ ላይ ሊከተል ከሚችል ሊደጋ ለመጠንቀቅ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይውሰዱ፣*

## ሰራተኞችንና ጎብኚዎችን በደንብ መመርመር

- ወደ ፋብሪካው በየዕለቱ የሚገቡትን ሰራተኞችንና ጎብኝዎችን በደንብ መርምሯቸው፤ የሚከተሉትን የቃል ምርመራዎችንን ጠይቋቸው፣
- እዚህ ፋብሪካ ውስጥ ለመጨረሻ ግዜ ከነበሩበት ግዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ ከታች ከተዘረዘሩት ማሳያዎች አንዱ ኣጋጥሞታልን? ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሚሰጡት መልስ "አዎን" ወይም "አይደለም" መሆን አለበት።
    - o አዲስ ትኩሳት (100.4 ፋራንሃይት ወይም ከዛ በላይ) ወይም የትኩሳት ስሜት ይሰማዎታልን?
    - o አዲስ ሳል?
    - o የትንፋሽ እጥረት?
    - o አዲስ የጉሮሮ መቁሰል?
    - o አዲስ የጡንቻዎች ህመም?
- በተገቢው ርቀትና ንጽህና በተመላበት ሁኔታ፡ ትኩሳት መለካት ከተቻለ ትኩሳት መለካት
- ሰራተኛው ከላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች **ለአንዱም ቢሆን** የሰጠው መልስ "አዎን" ከሆነ **ወይም** በአፍ ወይም በጆሮ ቴርሞሜትር ተለክቶ ትኩሳቱ ከ**100.4° በላይ** መሆኑ ከተረጋገጠ፣ በፋብሪካው ነርስ በተጨማሪ መታየት አለበት፣ነርስዋ ቤት ሂዶ ማረፍ ወይም ወደ ሆስፒታል መሄድ እንዳለበትና እንደሌለበት ትወስናለች። በተጨማሪም ሰራተኛው ቤት ከሄደ ከተቀሩት የቤተሰቦቹ አባላት ገለል ብሎ መቀመጥ እንዳለበት ልትወስን ትችላለች፣ ከአካባቢው የህዝብ ጤና ጥበቃ ክፍል ደግሞ የመኖርያ ቤትም ሆነ ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች እርዳታ ማግኘት እንዲችል ትጠይቃለች።

## ጽዳትና የጀርም መከላከያ ማድረግ

- በጋራ የሚሰሩባቸውን ቦታዎችንና መሳርያዎችን ቢያንስ ቢያንስ በየቀኑና አዲስ የሰራተኞች ሽፍት በሚቀየርበት ግዜ የጀርም መከላከያ በመነስነስ ክፍሉን ሙሉ በሙሉ ማጽዳት። መሳርያዎችና ቦታዎች ላይ የጀርም መከላከያ ሲነሰንሱ፣ በአካባቢ ጥበቃ ተቋም (Environmental Protection Agency (ኢ-ፒ-ኤ EPA) )የተመዘገቡትን የጀርም መከላከያዎች ተጠቀሙ።
- ሰራተኞች እረፍት የሚወስዱባቸው ቦታዎች፣ የመጸዳጃ ቤቶችና የምግብ መብያ ቦታዎች ሁሉ ከላይ እስከ ታች መጽዳትና በላያቸው ላይ የጀርም ማስወገጃ መድሃኒት መነስነስ ስላለበት፣ በንጽህና ስራ ላይ የሚሰታፉ የሰራተኞችን ቁጥር መጨመር
- አንድ ሰራተኛ ስራ ቦታው ላይ እንዳለ ቢታመም፣ በነበረበት የስራ ቦታ ላይ ሌላ ሰራተኛ ከመተካቱና ስራውን ከመጀመሩ በፊት፤ የታመመው ሰራተኛ የነበረበት ቦታ ወድያውኑ በደንብ መጽዳት አለበት።
- ጽዳቱና የጀርም መከላከያ መድሃኒቱ በተሰጠው መመርያ መሰረት በትክክል በስራ ላይ መዋሉን ተከታተሉ።
- በተለይ ብዙ ንክኪት የሚደረጉባቸው ቦታዎች ማለት ደረጃ ሲወርዱና ሲወጡ በቀኝና በግራ በኩል ያሉት የመደገፍያ ብረቶች፣ እንደ አጥር ሁነው የሚያገለግሉ መከላከያዎች፣ የስራ መሳርያዎች፣ የበር መክፈቻ እጀታዎችና ኮምፑተሮች...ወዘተ ልዩ ግምት ሊሰጣቸው ይገባል።
- የተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥር ክፍል (ሲ-ዲ-ሲ CDC) የሚከተሉትን መመርያዎች አውጥቷል፣ የስራ ቦታዎችን ስለማጽዳትና የ ጀርም መከላከያ መድሃኒት ስለ መርጨ፣ ፡[www.cdc.gov/coronavirus/2019- ncov/prepare/disinfecting-building-facility.html](www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/prepare/disinfecting-building-facility.html) ይጎብኙ።
- አስፈላጊነት ባለበት ቦታ ሁሉ የስራ ቦታው በደንብ አየር የሚገባበት መሆኑና የአየር መቆጣጣርያ ካስፈለገ እንዳለው መከታተል።

## አንዱ ከሌላው መራቅ

- ከእርስ በርስ የመራቅ መመርያን በፋብሪካው በተግባር እንዲተረጎም ማድረግ
- ከእርስ በርስ ቢያንስ የ6 ጫማ ርቀት ማድረግ እንደሚገባ የሚያመለክተውን የሲ-ዲ-ሲ- (CDC) መመርያን መከተል እንዲሁም ውጤታማ በሆነ መንገድ፣ የግል መከላከያዎችን እንደ ማስክ (የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጨርቅ)፣የፊት መሸፈኛዎችን ማድረግ

- ከእርስ በርስ ቢያንስ የ6 ጫማ ርቀት ላይ ሆኖ መስራት የማይቻል ከሆነ አንዱን ሰራተኛ ከሌላው የሚከላከል እንደ መስተዋት የመሰለ፣ እርስ በርስ ለመተያየት የሚያስችል ግን ከጀርምና ከሌላ ነገር የሚከላከል (መጋረጃ) በእያንዳንዱ ሰራተኛ መካከል ማድረግ
- በእያንዳንዱ ሰው ማህል ቢያንስ የ6 ጫማ ርቀት መኖር አለበት የሚባለውን መመርያ በስራ ለመተርጎም የተለያዩ መውጭያና መግብያ እንዲኖሩ ማድረግ
- የኮቪድ-19 (COVID-19) በሽታ ምልክት ላሳዩ ሰራተኞች ማቆያ የሚሆን ልዩ ቦታ መመደብ- ይህም ጂምናስቲክ ይሰራበት የነበረ ቦታ፣ የመጀመርያ እርዳታ የሚሰጥበትና ሌላ ሰው ለመግባት የተከለከለበት ቦታ ሊሆን ይችላል።
- ሰራተኞች በብዛት በሚሰበሰቡባቸው ቦታዎች ለምሳሌ ስራ ሲገቡ በስንት ሰዓት እንደገቡ ለማሳየት በሚፈርሙበት ቦታ፡ጤንነታቸውን ለመታየትም ሆነ እጃቸውን ለመታጠብ፣ እንዲሁም ማጓጓዥያ ለመጠበቅ በሚቆሙባቸው ቦታዎች ሁሉ ከእርስ በርስ ቢያንስ ስድስት ጫማ ርቀው የሚቆሙባቸው ቦታዎች ላይ ምልክት ማድረግ
- ከእያንዳንዱ ሰራተኛ መቀመጫ 6-ጫማ የሚርቅ ቦታ ላይ መስመር ማድረግ
- ስብሰባዎች በሚካሄዱባቸው ቦታዎች እያንዳንዱ ወንበር ወይም ሰው ከሌላው 6-ጫማ ርቀት ላይ እንዲሆን ማድረግ
- ሰራተኞች እንዳይጠጋጉ የተመደበላቸውን ርቀትና በየግዜው እጃቸውን የመታጠብ መመርያዎችን ማክበራቸውን የሚያረጋግጥ ሰው መመደብ
- ሰራተኞች በስራ ላይ እያሉ ከእርስ በርስ ለመለያየት የተደረጉ ጋሬጣዎች በደንብ እየጸዱና የጀርም መከላከያ መድሃኒቶች ተረጭቶባቸው መሆኑን በቀጣይነት መከታተል።

## ምርት፡ የስራ ሰዓትና የእረፍት ግዜ ሰዓቶች

- ሰራተኞች ለአንድ ነገር በሰልፍ ሲቆሙ፡ አንዱ ከሌለው በርቀት የሚቆምበትን ሁኔታ በማስተካከል ፍጥነት ያለው ስራ እንዲሰራ ማድ
- ሰራተኞች የስራ ልብስ በሚቀይሩበት፣ በመግብያዎች፣ ማጓጓዥያ በሚጠብቁባቸውና፣ ጤነታቸው በሚመረመርበትና ስራ መግባታቸውን በሚፈርሙበት ቦታዎች የሰው ብዛት ወይም ክምችት እንዳይኖር፡ የስራ ሰዓቶችን ማሸጋሸግ/ መቀያየር
- በየምግብ ቤትና በእረፍት ቦታዎች አንድ ላይ የሚሰበሰበው ሰው እንዳይበዛ የእረፍት ሰዓቶችን እንደገና መከለስ
- ምግብ የሚበላባቸውን ቦታዎች ወይም እረፍት የሚወሰድባቸውን ቦታዎች ቁጥር መጨመር

## የግል መከላከያዎችና የፊት ሽፋኖች (Personal protective equipment (PPE)

- ሁሉም ሰራተኞች፣ መደበኛ ከሆነው የግል መከላከያ ሌላ፣  በጥጥ የተሰራ አፍንጫና አፍ የሚሸፍን ማስክ፣ ከተጠቀሙበት በኋላ ወድያውኑ የሚጣል ወይም ዘላቂነት ያለው የፊት መሸፈኛ እንዲያደርጉ ማዘዝ፣
- ፊት ላይ የሚደረጉ የማጣርያ ማስተንፈሻዎች መጠቀምን መወሰንና በሌሎች ፊትን በሚሸፍኑ የኮቪድ-19 ( COVID-19 ) መቆጣጠርያ ዘዴዎች መተካት
- አስፈላጊ የሆኑ ወይም እንዲደረጉ የሚጠየቁ የግል መከላከያ መሳርያዎችና ትምህርቶች በሙሉ በቀጣሪዎች የሚከፈሉና የሚቀርቡ ናቸው

## የግል ንጽሕና

- ሰራተኞች ወደ ስራ ሲገቡና ከስራ ሲወጡ፣ ከመታጠብያ ቤቶች ሲገቡና ሲወጡ፣ ከመብላታቸውና ከመጠጣታቸው በፊትና በኋ እንዲሁም ሊበከሉ የሚችሉ ነገሮችን ከነኩ በኋላ እጃቸውን በደንብ እንዲታጠቡ ትእዛዝ መስጠትና በቂ ግዜ እንዲያገኙ ማድረግ
- ሰራተኞች በብዛት አንድ ቦታ ላይ እንዳይረባረቡ ፣ በቂ የእጅ መታጠብያ ቦታዎች በቀላሉ እንዲያገኙ ማድረግ
- ለእጅ መታጠብያ የሚሆኑ አያሌ ሳሙናዎችና የእጅ ማድረቅያዎችን ማቅረብ
- ከቦታ ወደ ቦታ ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ የእጅ መታጠብያዎች እንዲኖሩ ማድረግ
- በስራ ቦታዎች የእጅ ማጠብያ መድሃኒት (sanitizer) እና ማድረቅያ በብዛት ማቅረብ
- ሰራተኞች ትክክለኛውን የማስነጠስና የማሳል አገባቦችን እንዲከተሉ ማዘዝ

## ግንኙነት

- ኮቪድ-19 (COVID-19)ን ለመከላከል ምን እርምጃዎች በመወሰድ ላይ መሆናቸውን በየግዜው በሚደረጉ ስብሰባዎች፣ ጽሑፍ በመለጠፍ፡ በኮምፑተር ፣ በተቋሙ ዌብሳይትና ገና ስራ ሳይጀምሩ በሰሌዳዎች በሚለጠፉ ማስታወሻዎች ሁሉም ሰራተኞች እንዲያውቁት ማድረግ
- በስራ ቦታ ውስጥ ሰራተኞች የኮቪድ-19 (COVID-19) ምልክቶችን ወይም ሌሎች አደገኛ ነገሮችን ካዩ ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችላቸውን ዘዴዎች ማመቻቸት
- ሰራተኞች የኮቪድ -19 (COVID-19) ምልክቶችን ካዩ ወደ ስራ ቦታ እንዳይመጡ ማስታወስ፣ የህመም ፍቃዳቸውን እንዲሁም ሌሎች ጠቀሜታዎችም ካሏቸው ሲታመሙ ሊጠቀሙባቸው እንዲሚችሉ ማስረዳትና መፍቀድ
- ሰራተኞች፣ በሚገባቸው ቋንቋ ፣ ስለ መመርያዎችና ስለሕመሙ ምልክቶች ፡ ስለ እጅ ቶሎ ቶሎ መታጠብ፤ በአጠቃላይ ጽዳት ስለመጠበቅና ሲታመሙ ቶሎ ሪፖርት ስለማድረግ መረጃ ማቅረብ

## የኮቪድ-19 (COVID-19) የአሰራር ዕቅድ ትምህርት

- ተቋሙ ሊከተለው ስለሚገባ የኮቪድ-19 (COVID-19) የአሰራር ዕቅድና ለኮቪድ -19 (COVID-19) የመጋለጥን ሁኔታ ለመቀንስ ስለሚወሰዱት እርምጃዎች ማለትም ምርት፡ እቀባ፡ ሰራተኞችንና ደህነታቸውን በተመለከተ ስለተደረጉ ለውጦች አስፈላጊውን ትምህርት መስጠትና ገለጻ ማድረግ፣
- የኮቪድ -19 (COVID-19) ቫይረስ የህመም ምልክቶች፡ እንዴት ከአንድ ሰው ወደሌላው እንደሚተላለፍ፡ ተገቢ የእጅ መታጠብ ንጽህና ፣ ለህመሙ ከመጋለጥ ሊያድኑ የሚችሉ የትንፋሽ አገባቦችና ሌሎች መከላከያዎችን በተመለከተ የሚያግዙ መረጃዎችን ማከል፣
- አስተዳዳሪዎችና ሓላፊዎች፣ የኮቪድ-19 (COVID-19) የስራ ዕቅድ ውጤታማ መሆኑንና አለመሆኑን በቅርብ ይከታተላሉ።

## የስራ ጉዞ

- በስራ ምክንያት የሚደረጉ ጉዞዎችን መቀነስ ወይም ማቋረጥ፣
- ስብሰባ ማድረግ ቢያስፈልግ በኮፑተር ወይም በስልክ ማድረግ

## ከሩቅ ሆኖ መስራት

- በስራ ቦታቸው ላይ ሳይገኙ፣ ከሩቅ ሆነው ስራቸውን መስራት የሚችሉ ሰራተኞች ከሩቅ እንዲሰሩ መፍቀድ፣
- አስፈላጊ ስራዎችን የሚሰሩ ካልሆኑ በስተቀረ በመስርያ ቤቱ ጽህፈት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የሰራተኞችን ቁጥር መቀነስ

## ጎብኚዎችን ማጉደል

- ጎብኚዎች በተቋሙ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ስለሁኔታቸው በቅርብ መከታተልና ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ኮቪድ -19 (COVID-19)በብዛት ወደ ተራጨባቸው ቦታዎች እንዳልተጓዙ ማረጋገጥ፣
- የሲ-ዲ-ሲ የአደጋ ግምገማ መመርያን (CDC risk-assessment guidance) በመከተል፡ አስፈላጊ በሆኑ የስራ ቦታዎች የጎብኚዎችን ቁጥር መወሰንና ጎብኚዎች በተቋሙ ውስጥ ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀሳቸውን መቀነስ

# ስራና የሰው ሃይል ጉዳዮች

## የስራ አመዳደብ ሁኔታ

- በዚህ በኮቪድ-19 (COVID-19) የወረርሽኝ/ተላላፊ በሽታ ወቅት፣ የስራ ሁኔታዎች እንዴት እንደሆኑ ለምሳሌ ሊቀየሩ የሚችሉ የስራ ሰዓቶች ካሉ፡ ቤት ሆኖ የመስራት አማራጭ ካለ፣ ስራ የማቆም ወይም የደሞዝ ለውጥ ካለ ለሰራተኞች ግልጽ ማድረግ፣
- በሰራተኞች ላይ፣ በማንኛውም ምክንያት፣ አድልዎ ማድረግ ተቀባይነት እንደሌለውና አድልዎ ከታየ ለአለቆች ወድያውኑ መነገር እንዳለበት ማስረዳት

## ማበረታቻ ፕሮግራሞች

- ሰራተኞች ሲታመሙ ለሌሎች በስራ ቦታ ለሚገኙ ሰራተኞች እናዳያስተላለፉ ከስራ ቀርተው ቤታቸው ውስጥ እንዲቆዩ የሚያበረታታ ፕሮግራም እንዲኖር ማድረግ፣
- ሰራተኞች ሲታመሙ ከስራ በመቅረታቸው የሚደርስባቸው ምንም ዓይነት መጥፎ ነገር እንደሌለ በደንብ ግልጽ እንዲሆንላቸው ማስረዳት

## ከስራ ሲቀሩ ደሞዝ ስለመከፈል ሁኔታ (ፒ-ቲ-ኦ PTO) ና በህመም ምክንያት ስለሚወሰድ ፈቃድ ያሉት መመርያዎች

- ሰራተኞች በበሽታ ምክንያት ደሞዝ እየተቀበሉ ከስራ ሊቀሩ በሚችሉባቸው የቀናት ቁጥር ላይ ማሻሻያዎች ማድረግ፣ ሲታመሙ ወይም በቤታቸው ውስጥ በኮቪድ-19 (COVID-19) የተያዘ ወይም ምልክት ያሳየ ሰው ካለ ሰራተኞቹ የፒ-ቲ-ኦ(PTO) ፈቃድ እንዲወስዱ መፍቀድ፣
- በዚህ በኮቪድ-19(COVID-19) የወረርሽኝ/ተላላፊ በሽታ ወቅት፣ በስራ ቦታ በሰዓት የመገኘት ጉዳይን ትንሽ ላላ ማድረግ፣
- ከስራ ለመቅረት የሓኪም ወረቀት ማግኘት የሚያስፈልግ ከሆነ፡ የስራ ፍቃዱን ለመስጠት፣ ሰራተኞቹ ከስራ ከመቅረታቸው በፊት ወረቀቱን እንዲያመጡ አለመጠየቅ

## የሕክምና እርዳታ

- ሰራተኞች ከኮቪድ-19 (COVID-19)ጋር በተሳሰረ ምክንያት፣ ሓኪም ማየት ቢያስፈልጋቸው፣ ሓኪም ለማየት ከኪሳቸው የሚከፍሉት ኮፔ (co-pay) እንዳይከፍሉ አንሱላቸው፣
- በስራው ቦታ የተመደበ/ች ነርስ በቦታው ከሌለ/ች ሰራተኛው ከሓኪሞች በስልክ እርዳታ የሚያገኙበትን ዘዴ ማመቻቸት፣
- በኮቪድ-19 (COVID-19) የታመሙ ሰዎች፡ የአጭር ግዜ የስንክልና ጠቀሜታ ለማግኘት፣ በአዘቦቱ ቀን የሚጠብቁበትን የአምስት ቀናት ቆይታን አንሱላቸው።

## መነጠል/መገለል (ለብቻ መሆን)

- የኮቪድ-19 (COVID-19) በሽታ ምልክት የሚያሳዩ ሰራተኞች ከሌሎች ሰራተኞች መለየት አለባቸው።
- በመስርያ ቤቱ ያለው የሰው ሃይል ክፍል፡ የታመመው ሰራተኛ ቤቱ የሚሄድበትን መንገድ ማመቻቸት አለበት።

## ሌሎች የእገዛ አገልግሎቶች

ከኮቪድ-19 (COVID-19) የተላላፊ በሽታ ጋር በተሳሰረ ምክንያት በሰራተኞች ላይ ሊደረስ ስለሚችለው ጭንቀትና የገንዘብ ችግር የእገዛ አገልግሎት ለማድረግ እንደምትችሉ ለሰራተኛው ግለጹ።

የምግብ እሽጋ ሰራተኞች መብት ህግ (The Packinghouse Workers Bill of Rights law)፣ የሚኖሶታ ሕጎች 179.86 (Minnesota Statutes 179.86)፣ አሰሪዎች፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የስራ ቦታና ስራውን በደንብ ለማከናውን የሚያስፈልጉ መሳርያዎችን ለሰራተኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያዛል። ማንኛውም ተቋም ያለው የአስተዳደር ክፍል፣ ሰራተኞቹንና የአካባቢውን ማሕበረሰብ  በደንብ የመያዝና የመንከባከብ ባህል የሚከተል ከሆነ፡ የሰራተኞችን ደህነንት የሚጠብቅ ጥሩና ደህነቱ የተሟላ ተቋም ለመንገባት ይጠቅማል።

## ለታመሙ ሰዎች ቤት የሚሰጡ ከሆነ በሽተኞች ከጤነኞች መለየት አለባቸው

- በቡድን የመቀመጥ ምርጫ እንዳለና እንደሌለ መወያየት፣ የተሻለው አማራጭ፣ አንድ የታመመ ሰው የራሱ የሆነ የግል መኝታ ቤትና መጸዳጃ ቤት እንዲኖረው ነው። ይህ የማይሆን ከሆነና ከአንድ በላይ በሽተኛ ሰራተኞች ካሉ፣ ካልታመሙ በሽተኞች በመለየት፣ የታመሙትን በሽተኞች በሙሉ፡ አንድ ላይ እንዲኖሩ ማድረግ ይቻላል። ያለው አማራጭ የታመሙትን በሙሉ አንድ ክፍል ውስጥ ማስቀመጥ ከሆነ፡ ክፍሉ ትልቅ ክፍልና ጥሩ አየር የሚገባበት ክፍል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የታመሙ በሽተኞች ባሉበት ክፍል ውስጥ፡ የአንዱ በሽተኛ አልጋ ከሌላው በሽተኛ አልጋ ቢያንስ እስከ 6 ጫማ ርቀት እንዲኖረው፣ የታመሙት (መጋረጃ በመሰለ) መከለያ እርስ በርስ እንዲለያዩና የበሽተኞች አስተኛኘት ደግሞ አንዱ በአልጋው ላይ ሁኖ በስተግርጌ እንዲተኛ፣ የሚቀጥለው ሰው ደግሞ በአልጋው በራስጌ እንዲተኛ ማድረግ ያስፈልጋል።
- በኮቪድ-19 (COVID-19) እንደተያዙ በምርመራ የተረጋገጠ ሰራተኞችንና እንዲሁ በሚያሳዩት ምልክት ሊይዛቸው ይችላል የተባሉትን ሰራተኞች መለያየት ያስፈልጋል።
- **ምንም እንኳን ተቋሙ በአዘቦቱ ቀን ለሰራተኞቹ መኖርያ ቤት የማይሰጥ ቢሆንም፣ እቤታቸው ውስጥ ለብቻቸው ተገለው መኖር ለማይችሉ በበሽታው ለተለከፉ ሰራተኞች፣ ግዚያዊ መኖርያ ቤት ለመስጠት ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።**
- ሰራተኛ ከታመመ ወይም በማገገም ላይ ከሆነ አስፈላጊውን እንክብካቤ ማድረግ ያስፈልጋል፣ አስፈላጊውን እገዛ ለማድረግ እርዳታ ካስፈለገ ደግሞ ከአካባቢው የጤና ጥበቃ ክፍል ጋር መገናኘት ያስፈልጋል።
- ሰራተኛው በጣም ከታመመና ዕድሜው 65 ወይም ከዛ በላይ ከሆነ ወይም ( ለምሳሌ የሳንባ በሽታ፡ የልብ ድካም በሽታ፡ የስኳር በሽታ፣ ካንሰር፡ወይም በሽታ የመከላከል ደካማ አቅም የመሳሰሉት) ከባድ የጤና ችግር ያለው ከሆነ ሓኪም መጥራት ያስፈልጋል።
- ሰራተኛው የሚያሳያቸው ምልክቶች እየተባባሱ ከመጡ፡ ሓኪም መጥራት ያሻል።
- ሰራተኛው የመተንፈስ ችግር ካለው፣ በደረቱ ላይ ቀጣይ የሆነ ሕመም የሚሰማው ከሆነ ወይም ሌላ አደገኛ ምልክት የሚታይበት ከሆነ 911 ደውሉ።
- ሲ-ድ-ሲ(CDC) የሰጣቸውን መመርያዎች መከተል ያስፈልጋል።

## አንድ ሰራተኛ በላቦራቶሪ ምርመራ በእርግጥ ኮቪድ- 19 (COVID-19) እንዳለበት ከተረጋገጠ ምን መጠበቅ ይቻላል?

- አንድ ሰራተኛ ኮቪድ-19 (COVID-19) በእርግጥ እንዳለበት በላቦራቶሪ ከተረጋገጠ የሚኖሶታ የጤና ጥበቃ ክፍል(Minnesota Department of Health (MDH) ወደ ታመመው ሰራተኛ ስልክ በመደወል ቃለመጠይቅ ያደርግለታል። በበሽታው የተያዘው ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዳይገናኝና ለ14 ቀናት ከቤት እንዳይወጣ ብቻውን እንዲሆን ሃሳብ ሊያቀርብለትም ይችላል።

## የታመመ ሰራተኛ መቼ ነው ወደ ስራ ቦታው መመለስ የሚችለው?

- በሽተኛው ከስራ ቀርቶ በቤት በሚያርፍበት ግዜ፡ ለሌሎቹ የቤተሰቦቹ አባላት እንዳያጋባባቸው፣ ከተቻለ የራሱ ክፍልና መጸዳጃ ቤት እንዲኖረው ያስፈልጋል። የታዩት ምልክቶች ሁሉ ቀስ በቀስ እየጠፉ ሲሄዱና ከታች የተዘረዘሩት በሙሉ እስኪሆኑ ድረስ ከሌላው ሰው ተነጥሎ ቤት ውስጥ መቆየት አለበት፣
  - ምልክቶች ሲሻሻሉ (አብዛኛውን ግዜ ይህ እስከ 14 ቀናት ይፈጃል) እና
  - ምልክቶች ከታዩበት ቀን አንስቶ ቢያንስ ሰባት ቀናት ሲያልፉ እና
  - (ምንም የትኩሳት ማስታገሻ መድሃኒት ሳይወስዱ) ቢያንስ ለሶስት ተከታታይ ቀናት ትኩሳት ሳይታይ ሲቀር

## የላቦራቶሪ ምርመራ ተደርጎ አለበት ያልተባለ ሰው ግን ምልክት የሚያሳይ የታመመ ሰው የስራ ጓደኞች ምን ማድረግ አለባቸው ?

- የስራ ጓደኞች ፡ በጤና ጥበቃ ክፍል(MDH) ተለይተው እንዲቆዩ ያልተደረጉና የበሽታው ከምልክቶች ከሆኑት ነጻ እስከሆኑ ድረስ በስራ ገበታቸው ላይ ሊገኙ ይችላሉ። ሆኖም ግን ለተቋሙ የተሰጡትን የጤና ጥበቃ መምርያዎች በቅርብ መከታተል ይኖርባቸዋል። ከላይ የተዘረዘሩትን የጤና ምርመራ፣ የትኩሳት መለኪያ እንዲሁም ማስክ ወይም መሸፈኛዎችን የማዘውተር መመርያዎችን ይመልከቱ።